# ፀረ ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና ቅፅ 1 ቁጥር 3 መስከረም 2015 ዓ.ም


## የፌደራል የሥነ - ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን የስራ ርክክብ አካሄደ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አዲስ ከተቋቋመው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሁለቱ ኮሚሽኖች የሥራ ኃላፊዎች እና የከተማ አስተዳደሩ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎች በተገኙበት የስራ ርክክብ አካሄደ፡ ፡

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236 መሰረት የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸውን የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲያቋቁሙ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የራሱን የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አቋቁሞ የስራ ኃላፊዎችን መድቧል፡ ፡

በዕለቱ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ እንደተናገሩት ለብዙ ጊዜያት ሲነሳ የነበረው የሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸውን ኮሚሽኖች እንዲያቋቁሙ ሲሆን ይህም መልስ በማግኘቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የራሷን የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አቋቁማለች፡፡





የስራ ርክክብ .... ወደ ገፅ 2 የዞረ

## ኮሚሽኑ በትምህርት ዘርፍ ለሚገኙ አገር አቀፍ የሥነ - ምግባርና ፀረ - ሙስና ስራ አስፈፃሚዎች ስልጠና ሰጠ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከ600 በላይ ለሚሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የትምህርት ዘርፍ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ አስፈፃሚዎች በዝዋይ/ባቱ በሚገኘው በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ከመስከረም 10-12/2015 ዓ.ም ስልጠናና ውይይት አካሄደ፡፡



በስልጠናው ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ እንደተናገሩት የሙስና መከላከል ጥናቶች ዘርፍ ተኮርና ሳይንሳዊ መንገድን ተከትለው ውጤት እንዲያመጡ በኮሚሽኑ በኩል ስራዎች መጀመራቸውን ገልፀው መድረኩም የዚያ ውጤት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሰው ሃብት ልማት፣ ስራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ/ር ነገሬ ሌንጮ እንደተናገሩት ትምህርት ለአንድ ሀገር እድገትና ብልፅግና ፅኑ መሰረት ነው፡፡ ትምህርትን በፍትሃዊነትና በጥራት ተደራሽ



ያደረጉ ሀገራት ከራሳቸው አልፈው ለሌሎችም መጠጊያ ሲሆኑ ታይተዋል፡፡ በኢትዮጵያም ትምህርትን በፍትሃዊነትና በጥራት ተደራሽ ለማድረግ አንደኛው ማነቆ በትምህርት ሴክተሩ የሚታዩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የትምህርት ዘርፉን በተመለከተ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን በዚህም በአሁኑ ወቅት ከ30 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች በየደረጃው በትምህርት ላይ እንደሚገኙ ገልፀው፤ በትምህርቱ ዘርፍ የጥራት እና የሥነ-ምግባር እጦት ችግር፣ የሀሰተኛ ሰነዶች ጥቅም ላይ መዋልን ጨምሮ በርካታ ችግሮች እንደሚታዩም ጠቅሰዋል፡፡



የትምህርት ውይይት... ወደ ገፅ 2 የዞረ

## ኮሚሽኑ ለሀገር መከላከያ ሠራዊትና ለጥምር ሀይሉ የደም ልገሳና የገንዘብ ድጋፍ አደረገ።

ኢትዮጵያን ለማፅናት፣ ሰላም ለማስፈን እና አንድነቷን ለማስጠበቅ በዱር በገደሉ እየተዋደቀ ላለው የመከላከያ ሰራዊትና ለጥምር ጦሩ መላው ኢትዮጵያዊያን ደጀንነታቸውን እያሳዩ ይገኛሉ፡፡ የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮችና ሰራተኞችም ደማቸውን በመለገስ ከሰራዊቱ ጎን መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡

የመከላከያ ሰራዊትና ጥምር ጦሩ የሀገሩንና የወገኑን ሰላምና አንድነት ለማስጠበቅ ህይወቱን ሰጥቶ ሀገሩን ሲጠብቅ እኛ ደግሞ ደም በመለገስ ከጎኑ መሆናችንን ማሳያ ነው በማለት የገለፁት ደም የለገሱ የኮሚሽኑ አመራሮችና ሰራተኞች ሲሆኑ ለመከላከያ ሰራዊቱና ለጥምር ጦሩ አቅማቸው የፈቀደውን ድጋፍ እንደሚያደርጉና የተቃጣብንን ችግር ለመቀልበስ መንግስትም ወደኋላ ሳይል ከነሰንኮፉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጦርነቱን መፍትሄ በመስጠት ወደ ልማታችን መመለስ ይገባል በማለት አሳስበዋል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በበኩላቸው የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስከበር ህይወቱን እየከፈለ ላለው የመከላከያ ሰራዊትና ጥምር ጦሩ የሲቪሉ ማህበረሰብ እያደረገ ያለው ድጋፍ ከሰራዊቱ መስዋዕትነት አንፃር ከብዙ በጥቂቱ ነው ብለዋል፡፡

ዶ/ር ሳሙኤል አክለውም ከዚህ ቀደም የነበሩ አባቶቻችን የሀገራቸውን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ያደረጉትን ትግል የአሁኑ ትውልድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ በግንባር ያለው የመከላከያ ሰራዊትና ጥምር ጦሩ ኃላፊነቱን እየተወጣ እኛ በበኩላችን ደግሞ በየስራችን በተሰጠን ተልዕኮ በአግባቡ ሥራችንን በመስራት ለሀገር መከላከያ ሰራዊቱ ድጋፍ ማድረግ አለብን፡፡



አሸባሪው ህውኃት ኢትዮጵያን በበላይነት በመራባቸው አመታት የህዝብንና የመንግስትን ሀብትና ንብረት ሲዘርፍ እንደነበር ኮሚሽነሩ አውስታውቀው የሌቦች የመጨረሻ እጣ ፋንታ ውርደትና ሽሽት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሌብነት ልማትን ወደኋላ የሚያንሸራትት በመሆኑ በ2015 ዓ.ም ሌቦችን የማጥራት አመት ይሆናል፡፡ የመንግስት ተቋማት የመንግስት አገልግሎትን በተቀላጠፈ ሁኔታ ማከናወን አለባቸው፡፡ ህዝብን ከመንግስት ጋር የሚያጣሉ ቦታ የላቸውም በማለት ኮሚሽነሩ ገልፀዋል ፡፡

የኮሚሽኑ አመራሮችና ሰራተኞች ለመከላከያ ሰራዊቱና ለጥምር ጦሩ ደም ከመለገስ ባለፈ ኮሚሽኑ የ1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) ብር የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡

ኮሚሽኑ ለጀግናው የሀገር መከላከያ ሠራዊትና ለጥምር ኃይሉ ያደረገውን የገንዘብ ድጋፍ የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ ለመከላከያ ሚኒስቴር ዴኤታ ለሆኑት ለወ/ሮ ማርታ ሎጂ አስረክበዋል፡፡

ከዚህ ባለፈም የኮሚሽኑ ሠራተኞች በሀገሪቱ ላይ የተቃጣውን የውሸት ዜናዎችና ዘገባዎች አፀፋዊ ምላሽ እንዲሰጡ ኮሚሽኑ የማስተባበርና የመከታተል ሥራዎችን እንደሚሰራም አስታውቋል፡፡

# የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንብን የጣሱ ከ1 ሺህ በላይ አመራሮችና ሠራተኞች ላይ እርምጃ ወሰደ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በተጠናቀቀው የ2014 በጀት ዓመት ደንብን የጣሱ ከ1 ሺህ በላይ በሚሆኑ አመራሮችና ሠራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰዱን ገለጸ።

አገልግሎቱ ደንበኞቹን እያማረረ ነው ያለውን ሌብነትን ለመቀነስና ከሙስና የጸዳ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት እያደረኩ ነው ብሏል።

የአገልግሎቱ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ እንደገለጹት ደንበኞችን በሚያጉላሉ አመራሮችና ሰራተኞች ላይ ጥብቅ ክትትል በማድረግ ጠንካራ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በዚህም ሌብነት፣ ብልሹ አሰራርና የዲስፕሊን ግድፈት ፈጽመው የተገኙት ላይ ከቃል ማስጠንቀቂያ እስከ ሥራ ማሰናበት እርምጃ መውሰዱን አቶ መላኩ ተናግረዋል። በዚህም 1 ሺህ 50 አመራርና ሠራተኞች አስተዳደራዊ ርምጃ የተወሰደባቸው ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 24ቱን ከኃላፊነት የማንሳትና 75ቱ ከሥራ መሰናበታቸውን ጠቅሰዋል። አገልግሎቱ በዘረጋው የቅሬታ መቀበያ ሥርዓት በመረጃ የተደገፉ ጥቆማዎች ከደረሱት በኅብረት ሥምምነትና የሥራ አመራር መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እርምጃዎችን የሚወስድ መሆኑን ጠቁመዋል።

አገልግሎቱ ብልሹ አሰራር እንዳይኖር ለመግታት ጥረት እያደረገ ቢሆንም ጥቂት አመራርና ሠራተኞች ከሕገወጥ ደላሎች ጋር በመመሳጠር ህብረተሰቡን እያማረሩ ነው ብለዋል። በዚህም ሆን ብሎ ኃይል በማቋረጥ ኅብረተሰቡ ገንዘብ እንዲያሰባስብና እንዲከፍል በማድረግ ኃይልን መልሶ የማገናኘት ህገወጥ ተግባር እየተፈጸመ ስለመሆኑ ጥቆማዎች እንደሚደርሷቸው ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ አገልግሎቱ ጠንካራ እርምጃ መውሰዱን የሚቀጥል ሲሆን፤ ህብረተሰቡ የራሱን መብት በገንዘብ አሳልፎ መሸጥ የለበትም ብለዋል። በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ ዝርፊያና ውድመት የሚደርሰው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሠራተኞች የደንብ ልብስ በለበሱ ዘራፊዎች መሆኑንም ጠቁመዋል።

ኅብረተሰቡ ኃይል ሲቋረጥና አጠራጣሪ ነገር ሲገጥመው በ905 ነፃ የስልክ መስመር እንዲሁም በየክልሉ ባሉ ዲስትሪክቶችና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ጽሕፈት ቤቶች ጥቆማውን መስጠት እንዳለበት ማሳሰባቸውን ከኢትዮጲያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡



# በትምህርቱ ዘርፍ የሚታዩ የሙስናና ብልሹ አሰራርን በተመለከተ ጥናት ቀረበ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ እያስከተለ ያለውን ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል ከተለመደው የአሰራር ጥናት በመውጣት ዘርፍ ተኮር የሆነና ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ የሙስና መከላከል ጥናቶችን በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ጥናት ከተካሄደባቸው መስኮች አንዱ የትምህርት ዘርፍ ነው፡፡

ጥናቱ ቀርቦ ሰፊ ስልጠናና ውይይት የተደረገበት ኮሚሽኑ ከ600 በላይ ለሚሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚገኙ የትምህርት ዘርፍ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ስራ አስፈፃሚዎች በዝዋይ/ባቱ በሚገኘው በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ከመስከረም 10-12/2015 በሰጠው ስልጠና ላይ ነው፡፡

ጥናቱ የትምህርት ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት የሙስና ሥጋት የሆኑ አሰራሮችን በመለየት፣ ደረጃ በመስጠት፣ ባህሪያትን በመፈተሽ፣ ሙስና የሚከሰትባቸውን የሥራ ክፍሎች እና የሙስና ምንጭና የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ በማወቅ የመፍትሔ ሐሳብ ያቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማም በትምህርት ሴክተሩ ውስጥ ያለውን የሙስና ስጋት በመለየትና በመመዘን የመፍትሄ ምክረ-ሃሳብ መስጠት ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በፌደራል ደረጃ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በመንግስትና በግል ዩኒቨርሲቲዎች፣ በፈተናዎች እና ምዘና አገልግሎት፣ በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ሆኖ በሁለት ክልሎች በኦሮሚያና ደቡብ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ በተመረጡ የትምህርት ተቋማት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ እንደሚያሳየው በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ብዛት ያላቸው የሙስና ስጋቶች የተለዩ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የመምህራን በተደጋጋሚ ከፍል አለመግባት፣ ህገ-ወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር እና ደረጃ ዕድገት፣ የአሰራር ግልጽነት መጓደል እና ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናወን የመንግስትንና የህዝብን ንብረት ለግል ጥቅም ማዋል፣ የተማሪ ዝዉዉርን በዘመድ





ጥናቱ እንደሚያሳየው በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ብዛት ያላቸው የሙስና ስጋቶች የተለዩ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የመምህራን በተደጋጋሚ ከፍል አለመግባት፣ ህገ-ወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር እና ደረጃ ዕድገት፣ የአሰራር ግልጽነት መጓደል እና ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናወን የመንግስትንና የህዝብን ንብረት ለግል ጥቅም ማዋል፣ የተማሪ ዝዉዉርን በዘመድ አዝማድ አና በጥቅም መስራት፣ ለተማሪ የማርክ ማጭበርበር መስራት፣ በመዝገብ/ሬጅስትራር ቤት በኩል ያላለፉ ተማሪዎችን እንዳለፉ ተደርጎ ሰርተፊኬት መስጠት በጥናቱ ከተገኙ ክፍተቶች መካከል ይገኙበታል፤ እንዲሁም ጥናቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊጋለጡ ይችላሉ የተባሉ የስራ ክፍሎችን የለየ ሲሆን ግዥ፣ ፋይናንስ፣ የሰው ሃብት ልማት እና የንብረት ክፍሎች ለሙስና የመጋለጥ ከፍተኛ ዕድል ያላቸው እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

ጥናቱ በትምህርት ተቋማት በሚካሄዱ የግንባታና ዕድሳት ተግባራት ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ አምስት የሙስና ስጋቶች የለየ ሲሆን በዚህም በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ

የትምህርት ጥናት ... ወደ ገፅ 2 የዞረ

## የስራ ርክክብ ...

ከገፅ 1 የቀጠለ




የከተማ አስተዳደሩም ኃላፊዎችን መድቦ ወደ ስራ ለመግባት ያደረገው ጥረት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ያለውን ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ያሳየበት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ምክትል ኮሚሽነሩ እንደገለፁት አዲስ አበባ ከተማ ሰፊ እና የብዙ ዓለማቀፍ ዲፕሎማቶች እንዲሁም የፌደራል መንግስት መቀመጫ ብትሆንም በውስጧ ከፍተኛ የሆነ ህብረተሰቡን ያማረረ ሙስናና ብልሹ አሰራር የሰፈነባት ከተማ እንደሆነች ጠቁመው ይህንን ችግር ለመታገል ደግሞ የራሷ የሆነ ኮሚሽን መቋቋሙ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ገለፃ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አዲስ አበባ ካላት ስፋት አንፃር የራሷ የሆነ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ለነዋሪዎቹዋ የምትመች ከተማ ለማድረግ ኮሚሽኑ መቋቋሙ ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቁመው፤ ነገር ግን የሚፈለግውን ውጤት ለማምጣት የሥነ-ምግባር አስፈፀሚ አካል ራሱን ከሙስና ማፅዳት እንዳለበት በማስገንዘብ የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንም አዲስ የተቋቋመውን ኮሚሽን በሚችለው ሁሉ ለመደገፍ ዝግጁ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አዲስ የተሾሙት የአዲስ አበባ ከተማ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኑን ለማገዝ ቁርጠኛ እንደሆነ ጠቅሰው ኮሚሽኑም ጠንካራ ተቋም ለመገንባት የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ የተለያዩ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች፣ የዲጂታላይዜሽን እና የመሳሰሉትን ተግባራት እያከናወነ እንደሚገኝ አስታውቀው በተጨማሪም ከፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ብዙ ልምዶችን በመውሰዱ ጠንካራ ተቋም ለመመስረት እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለአዲስ አበባ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አቶ ጀማል ረዲ በዋና ኮሚሽነርነት፣ አሰግደው ኃ/ጊዮርጊስ እና አሰፋ-ቶላን በምክትል ኮሚሽነርነት ሾሟል፡፡

## የትምህርት ውይይት ....

ከገፅ 1 የቀጠለ

ዶ/ር ነገሬ አክለውም የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች በእውቀት ላይ በመመስረት ችግሮችን በመለየት እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ መፍታት እንዲሁም ትክክለኛ መረጃን በመያዝ ከሚዲያ ተቋማት ጋር አብሮ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር በበኩላቸው ባስተላለፉት መልዕክት መንግስት ሌብነትን ቀይ መስመር አድርጎ መውሰዱን ገልጸው ሙስናን ለመከላከል የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለውጥ ለማምጣት ደግሞ የትምህርቱ ዘርፍ ዋነኛ መሳሪያ መሆኑን ጠቅሰው ኮሚሽኑ ሙስናን ዘርፍ ተኮር በሆነ መንገድ ጥናት በማካሄድና በመከላከል ሀገራዊ የሆነ አቅም ለመገንባት እየሰራ ይገኛል፡፡ ዶ/ር ሳሙኤል አክለውም በትምህርት ዘርፍ ከሚገኙ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ አስፈፃሚዎች በዕውቀትና በትክክለኛ መረጃ ላይ በመመስረት እንዲሁም ነፃና ገለልተኛ በመሆን በተቋማቸው የሚታዩ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመለየት እንዲሁም ስራው ትግል የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

በስልጠናው ላይ ኮሚሽኑ ያስጠናው በትምህርት ሴክተሩ የሚታዩ የሙስና ስጋ ተጋላጭነት ጥናት ቀርቦ ሰፊ የሆነ ውይይት እና ምክክር ተካሂዶበት ከሰልጣኞችም ለቀጣይ ተግባራት የሚያግዙ ግብዓቶች ተሰብስበዋል፡፡

## የትምህርት ጥናት ....

ከገፅ 2 የቀጠለ

እንዲካሄድ መፍቀድ፣ በጨረታ ጊዜ ብቃት የሌለዉ ተቋራጭ ጨረታዉን እንዲያሸንፍ ማድረግ እና ጨረታዉ ከተጠናቀቀና አሸናፊዉ ከተለየ በኋላ በግዥና በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ የግንባታ ግበአቶች ስራ ላይ እንዲዉሉ መፍቀድ ይገኙበታል፡፡

በየሴክተሩ ከተለዩ የሙስና አይነቶች መካከል እያንዳንዱ ተቋም የሚመለከተውን የሙስና ስጋት አይነት ለይቶ መውሰድ፣ ተለይተው የወጡ ስጋቶችን መነሻ በማድረግ የመፍትሄ ስትራቴጂ በማዘጋጀት አመራሩ ቀዳሚውን ተነሳሽነት በመውሰድ ስትራቴጂውን ለመተግበር መንቀሳቀስ፣ ስትራቴጂ ሲነደፍም ሆነ ወደ ተግባር ሲኬድ በተቻለ መጠን ቴክኖሎጅን ለመጠቀምና ዘላቂ አሰራር መዘርጋት ላይ ትኩረት ማድረግ፣ ሁሉም የሴክተሩ ተቋማት ጥናቱን መነሻ በማድረግ የራሳቸውን የስጋት ትንተና በየጊዜው ቢያደርጉ ሙስናን ለመከላከል አቅም በመገንባት የመከላከል ስራ የአንድ ወቅት ስራ ሳይሆን ዘላቂነት ያለው ጥረትን የሚጠይቅ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

# ኮሚሽኑ በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ ከሚገኙ የሥነ - ምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋር ስልጠናዊ ውይይት አካሄደ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሀገር-አቀፍ የገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ ለሚገኙ ከ400 በላይ ለሚሆኑ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎችና ባለሙያዎች በዘርፉ የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል አሰራር ላይ ከመስከረም 24 እስከ 25/2015 ዓ.ም በሀዋሳ ከተማ በሚገኘው ሳውዝ ስታር ሆቴል ለሁለት ቀናት ስልጠናዊ ዉይይት አካሄደ፡፡





የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ እንደገለፁት አሁን ባለንበት ወቅት ሙስና ሰላማችንና አንድነታችንን እየተፈታተነ ያለ ችግር ነው፡፡ ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ የቆየ ቢሆንም ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አንፃር ግን ገና እጅግ ብዙ ተግባራት ይቀሩታል፡፡ በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ አሰራሩ ላይ ሪፎርም በማድረግ የሙስና መከላከል ጥናቱን ዘርፍ ተኮር በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍም አንዱ ተለይቶ ጥናት የተካሄደበት ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው ከዛሬው ስልጠናና ውይይት በርካታ ግብዓቶች እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡



በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ደሳለኝ ወዳጆ ባስተላለፉት መልዕክት ሙስና አሁን ሀገራችን ያለችበት ዋነኛ የችግር ምንጭ መሆኑን ጠቁመው በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ የሚሰበሰቡ የሀገሪቱ የገንዘብ ምንጮችን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የኮሚሽኑ ተግባር ብቻ ሳይሆን የሁሉም አጋር አካላትን ርብርብ እንደሚጠይቅ ጠቅሰው ኮሚሽኑ አሁን የጀመረው ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስራ ሊበረታታ እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

ኮሚሽኑ ያስጠናው በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ዳሰሳ ጥናት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቀበታ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ሚንስትር ወ/ሮ አይናለም ንጉሴ፣ የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ እንዲሁም ኮሚሽኑ ያስጠናውን ጥናት ካጠኑት ባለሙያዎች መካከል አንዱ የሆኑት ዶ/ር ኢማኑኤል ገብረ ዩሐንስ ተገኝተው ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያዎችን ሰጥተዋል፡፡

ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ገለፃ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናት ወረቀት ላይ ብቻ የሚቀር መሆን እንደሌለበት እና የተጠኑ ጥናቶችን ተቋማት ወደራሳቸው ወስደው መጠቀም እንደሚጠበቅባቸው አመላክተዋል፡፡ በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ የሚገኙ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎችም በየተቋማቸው ነፃና ገለልተኛ ሆነው መረጃን መሰረት በማድረግ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ሳይንሳዊ ጥናት በማካሄድ በተቋሙ የሚታዩ የሙስና ስጋቶችን መለየትና መፍትሄዎችን በማስቀመጥ ተግባራዊነቱን መከታተል እንዳለባቸው ጠቁመው በገቢዎችና ጉምሩክ ዙሪያ ያሉ አመራሮች ሙስናን ለመከላከል የሚያሳዩትን ቁርጠኝነት እንደሚያደንቁ ገልፀዋል፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቀበታ በሀገር አቀፍ ደረጃ ዘርፍ ተኮር የሆነ ሙስና የመከላከል ስራ ትልቅ አቅምን የሚጠይቅ መሆኑን ጠቁመው ኮሚሽኑ የጀመረው ስራ ሊበረታታ እንደሚገባው እና ለሙስና ትግሉ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ገልፀዋል፤ ፈፃሚው አካልም ለስራው ከልብ በመነጨ በትጋት መስራት እንደሚገባው እና ሙሰኞች ተደራጅተው የሚሰርቁ በመሆናቸው ስራውን የሚሰራው አካልም ተደራጅቶ በትብብር ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚንስትር ወ/ሮ አይናለም ንጉሴ በበኩላቸው ሙስና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረቀቀ የመጣ መሆኑንን ጠቁመው ሀገራችን ባለብዙ ዘርፍ ኢኮኖሚ አማራጭ ያላት ሀገር ብትሆንም ኢኮኖሚው በሚፈለገው ደረጃ እያደገ ላለመሆኑ ሌብነት አንዱና ዋነኛው ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ የሀገርን እድገት ለማስቀጠል እና ጠንካራ መንግስት ለመፍጠር የሚረዳ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው በእነዚህ ዘርፎች የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችንና ሙስናን መከላከል የሁሉንም አጋዥ አካላት ርብርብ ይጠይቃል፡፡ ሚኒስትርዋ አክለውም ኮሚሽኑ ጥናቱን ማስጠናቱን አድንቀው የቀረቡትን ችግሮች በመውሰድ ተቋሙ ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት የሚያደርግ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በሕግ ጥላ ስር በሚገኙት የፍትሕ ሚኒስቴር ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ እና ሌሎች 2 የወንጀል ተሳታፊዎች ላይ ክስ ተመሰረተ

ዐቃቤ ሕግ ከሙስና ወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ፈይሳ ሾርኬ ሳፋዎ በፍትሕ ሚኒስቴር የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ 2ኛ ተከሳሽ አቶ አለማየሁ ታደሰ ከበደ በፍትሕ ሚኒስቴር የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዐቃቤ ሕግ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሻ አቶ ፍሬው በቀለ ታየ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታገደውን እግድ እናስነሳልሃለን፤ በዋስም እንድትወጣ እና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች እንዳይቀርቡ በማድረግ ክሱ እንዲቋረጥ እናደርጋለን በማለት ገንዘብ ጠይቀዋል፤ ተቀብለዋል በሚል የሙስና ወንጀል ክስ መስርቷል፡፡

የዐቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያስረዳው ተከሳሾች በጥቅም በመመሳጠር የማይገባ ጥቅም ለራሳቸው ለማግኘትና ለሌሎች ሰዎችም ለማስገኘት በማሰብ የግል ተበዳይ አቶ አረጋይ ግርማይ በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 03 የሚገኝ ኤም. ኤ ሆቴል ኃ/የተ/የግ/ማ የተባለ ድርጅቱን ለ2ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ለመሸጥ ፈልጎ ሆቴሉ ከሙስና ወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታገደ በመሆኑ ምክንያት እግዱ እንዲነሳ እናደርጋለን በማለት የግል ተበዳይ ገንዘብ እንዲከፍል ጠይቀዉት፣ የግል ተበዳይ በበኩሉ እግዱ በሌላ ክርክር በፍርድ ቤት የተነሳ በመሆኑ ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ በመሆኑ፣ ተከሳሾች በጥቅም በመመሳጠር የተጠየቀዉን ገንዘብ እንዲከፍል በማስገደድና በማሳመን በአጠቃላይ የግል ተበዳይ በ3ኛ ተከሳሽ በኩል 7,800,000 ብር እንዲከፍል በማድረግ ብር በመቀበላቸው ሶስቱም ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን በፈፀሙት በስልጣን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

በዚሁ የክስ መዝገብ በ1ኛ ተከሳሽ ተከሳሽ ላይ በቀረበ 2ኛ ክስ ተከሳሽ የተቀበለው ገንዘብ በወንጀል የተገኘ መሆኑን እያወቀ ገንዘቡን በራሱ ስም ቢቀበልና ገቢ ቢደርግ ወንጀሉ ሊደረስበትና የህግ ተጠያቂነት እንደሚመጣበት በማሰብ በወንጀል ድርጊት ያገኘውን ገንዘብ ህገወጥ ምንጩን፣ ዝውውሩን ወይም የባለቤትነት መብቱን የደበቀ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው

በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ተከሷል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ቀርቦ ያቀረበውን የዋስትና ጥያቄ እና የዐቃቤ ሕግን ተቃውሞ መርምሮ ብይን ለመስጠት ለመስከረም26 ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ እንደተሰጣቸው ከፍትህ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡

# በአገራዊ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ ከ42 ሚሊዬን ብር በላይ ማዳን ተቻለ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና ከመከሰቱ በፊት የመከላከል ሥራ መሥራት ይቻል ዘንድ በ2015 በጀት ዓመት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል የሚያስችል ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በተቋማት ከተደረጁ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎችን አቅም የመገንባት ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ በተቋማቸው የሚታዩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ከመከሰታቸው በፊት ቀድሞ በመድረስና በመከላከል የመንግሥትና የህዝብ ሀብት ለማዳን ባስቀመጠው ግብ መሰረት በተቋማት ላይ ስራዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ከ20 የፌዴራል የመንግሥት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች እና በ7 ክልሎች፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ የኦሮሚያ ክልል፤የሐረሪ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ሲዳማ ክልል፤ደብብ ብ/ብ/ህ/ክልል እና ሶማሌ ክልል ውስጥ በተሰሩ አገራዊ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራዎች 42,447,016.66 (አርባ ሁለት ሚሊዬን አራት መቶ አርባ ሰባት ሽህ ከአስራ ስድስት በር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም)ብር ማዳን የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም በተለያዩ ተቋማት ውስጥ በነበረው ማጣራት የባከኑ የመንግሥት ንብረቶች እንዲመለሱና አግባብ ያልሆኑ አሰራሮች ማስተካከያ እንዲደረግባቸው እንዲሁም የሠራተኞች ዝውውርና የዕድገት ውሳኔዎች ያለአግባብ የተፈፀሙ በመሆናቸው እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሩብ ዓመት የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ ከተካሄደባቸው ተቋማት መካከል የጉምሩክ ኮሚሽን፣ የንግድ ስራዎች ኮፖሬሽን፣ የደብረ ብርሃን ዩንቨርሲቲ፣ የደብረ ታቦር ዩንቨርሲቲ፣ የወልድያ ዩንቨርሲቲ እንዲሁም የብርሃንና ሰላም ድርጅት፣ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሆኖ ከክልሎች የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ የኦሮሚያ ክልል፣ የሐረሪ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የሲዳማ ክልል፣ የደብብ ብ/ብ/ህ/ክልል እና የሶማሌ ክልል በራሳቸው አቅም የተሰሩ የአስቸኳይ የሙስና መከላል ሥራዎች ሲሆኑ የተቀሩት በፌደራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተሰሩ ሥራዎች ናቸው፡፡

በተቋማቱ ላይ በቀረበ ጥቆማዎች በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ ተደርጎባቸው እንዲስተካከሉ ከተደረጉ ጉዳዮች መካከል ስልጣንን አላአግባብ መጠቀም፣ ከባድ እምነት ማጉደል፣ በተጋነነ ዋጋ ሊፈፀም የነበረ ግዥ እና ጨረታ እንዲሁም ያለአግባብ ደረጃ እድገት መስጠት ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ሩብ ዓመት በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ ሪፖርት ከሚጠበቀው የሙስና መከላከል የትኩረት ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ገቢ እንዲያደርጉ ከሚጠበቁት መካካል 8% ብቻ በመሆኑ በዚህ ዙሪያ በሚቀጥሉት ሩብ ዓመታት ከሁሉም የሙስና መከላከል ዘርፎችና ከክልል የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ከፍተኛ ሥራ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ርዕሰ-አንቀፅ

የምርመራ ጋዜጠኝት በአንድ ለምርመራ በተመረጠ ጉዳይ ላይ በደንብ ዝግጅት በማድረግ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አጣርቶ እውነቱን በማውጣት ለማህበረሰቡና ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ ነው፡፡ ባለንበት ወቅት በየትኛውም ዓለም ሶስት የመንግስት አካላት ያሉ ሲሆን እነዚህም ህግ አውጪ፣ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈፃሚዎች ናቸው፡፡ ባለንበት ወቅት ደግሞ ሚዲያ አራተኛውን ደረጃ ይዟል፡፡

የምርመራ ጋዜጠኝነት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ሚናው እጅግ የጎላ ነው፡፡ በመልማት ላይ ባሉ ሀገራት የሙስና ወንጀል እጅግ ውስብስብ ቀውሶችን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በሀገራችን አሁን ላይ የሚታዩት ውስብስብ ቀውሶች ከዚሁ ከሙስና ወንጀል ጋር ተያይዞ የተከሰቱ ናቸው፡፡ የሙስና ወንጀል እጅግ ውስብስብ መንገድን የተከተለ፣ በርካታ ሰዎች የሚሳተፉበት፣ የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶች ጥቅም ላይ የሚውሉበት የተወሳሰበ የወንጀል ዓይነት ነው፡፡

የምርመራ ጋዜጠኝነት ደግሞ በተቋማት የሚከሰቱ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አንፃር ዓለም ላይ በስፋት ተግባራዊ እየተደረገ ያለና ለውጥም ያመጣ የጋዜጠኝነት አንዱ እና ዋነኛው ክፍል ነው፡፡ የምርመራ ጋዜጠኝት መነሻ ሀገር አሜሪካ ስትሆን ለዚህም ዋነኛው መነሻው "የወተርጌት ቅሌ" የሚባለው ከመርጫ ጋር ተያይዞ የተከሰተን የሙስና ወንጀል በምርመራ ጋዜጠኝነት የተጋለጠበት ሲሆን ከዚያ መነሻ በኋላ ዓለም ላይ በርካታ ለውጥ ያመጡ የምርመራ ጋዜጠኝነት ሪፖርቶች ተሰርተው በመውጣታቸው በርካታ ለውጦችን አምጥተዋል፡፡ በእኛ ሀገርም ጅምር ተግባራቶች አሉ፡፡ ነገር ግን በሀገራችን አሁን ከሚታዩ በርካታ የሙስና ወንጀሎችና ብልሹ አሰራሮች ጋር ሲነፃፀር እጅግ ብዙ ስራዎች እንደሚቀሩ በግልፅ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር በርካታ ተግባራቶችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ይህ ተግባሩ የሁሉንም ባለድርሻ አካላትን እርብርብ የሚጠይቅ ሀገራዊ አጀንዳ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ኮሚሽኑ የምርመራ ጋዜጠኝት እንዲያድግና የሚዲያ ተቋማትም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፉ በተለያዩ ወቅቶች ከምርመራ ጋዜጠኞችና ከሚዲያ ተቋም ኃላፊዎች ጋር ምክክር አድርጓል፡፡

ፀረ-ሙስና፤ በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

አድራሻ
ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች www.feaccdars.gov.et

ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5lGXTSIYUMPBF1

# ቆይታ

የምርመራ ጋዜጠኝነት (investigative Journalism) ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ሚናው እጅግ የጎላ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዛሬው ቆይታችንም ከዶ/ር ሳምሶን መኮንን በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የህዝብ ግኑኝነትና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር እና ከዶ/ር ጌታዋ ሞላ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮፖሬት የስልጠና ጥናት ተቋማ ም/ኃላፊ እና ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሚተላለፈው የዐይናችን ፕሮግራም አዘጋጅነት እና በቡድን መሪነት ያገለገሉ ናቸው፡፡ አጠቃላይ የምርመራ ጋዜጠኝነት (investigative Journalism) ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ያለውን ፋይዳ እንዲሁም በተግባር ያመጣውን ለውጦች በተመለከተ ያደረግነውን ቆይታ ለአንባቢያን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

## “የምርመራ ጋዜጠኝነትን ውጤታማ ለመድረግ ጋዜጠኛው በራሱ ከሙስና የፀዳ ሊሆን ይገባዋል ! ”



ዶ/ር ሳምሶን መኮንን በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የህዝብ ግኑኝነትና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር

➢ የምርመራ ጋዜጠኝነት (investigative Journalism) ስንል በዋናነት ምን ማለታችን ነው? ከተለመደው የጋዜጠኝነት ሙያ በምን ይለያል? በሚል ላቀረብንላቸው ጥያቄ መልስ የሰጡት ደ/ር ሳምሶን፡- ጋዜጠኝነት ስንል በራሱ ብዙ ዓይነት ሙያዎችን በውስጡ የያዘ ሲሆን ከእነዚያ ውስጥ የምርመራ ጋዜጠኝነት (investigative Journalism) አንዱ ነው፡፡ የምርመራ ጋዜጠኝነትን በአጭሩ ለመግለፅ ያህል በአንድ ለምርመራ በተመረጠ ጉዳይ ላይ በደንብ ዝግጅት በማድረግ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አጣርቶ እውነቱን በማውጣት ለማህበረሰቡና ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ ነው፡፡ ባለንበት ወቅት በየትኛውም ዓለም ሶስት የመንግስት አካላት ያሉ ሲሆን እነዚህም ህግ አውጪ፣ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈፃሚዎች ናቸው፡፡ በአራተኛነት ደግሞ ሚዲያ እንደተቀመጠ ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ ሶስት የመንግስት አካላት የተሰጣቸውን ስልጣንና ኃላፊነት በትክክል እየተወጡት መሆኑን ሚዲያው በምርመራ ጋዜጠኝነት በኩል ያረጋግጣል፡፡

በዚህ የምርመራ ሂደት ውስጥ ነው እንግዲህ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚፈተሹት፡፡ የምርመራ ጋዜጠኝነት የአንድ ሀገር የመንግስት አካል በህገ-መንግስቱ መሰረት የተሰጠውን ኃላፊነት ህግና ደንቡ በሚፈቅድለት መሰረት ነው እያከናወነ ያለው ወይስ ከህግና ደንብ ውጪ ነው እየተሰራ ያለው የሚለውን ይመረምራል፤ ያጋልጣል፤ የመፍትሄ አቅጣጫዎችንም ያስቀምጣል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ በስፋት እየተሰራበት የመጣው የጋዜጠኝነት ዓይነት የምርመራ ጋዜጠኝነት ሲሆን ብዙ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችም በማጋለጥ ላይ ይገኛል፡፡ የምርመራ ጋዜጠኝነት (investigative Journalism) ክህሎት፣ አቅምና ሀብትን የሚጠይቅ ስራ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

➢ የምርመራ ጋዜጠኝነት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ፋይዳውን ዶ/ር ሳምሶን ሲያብራሩ እንደገለፁት የምርመራ ጋዜጠኝነት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ያጋልጣል፡፡ በእርግጥ ሙስናን መመርመር የፖሊስና የዐቃቤ-ህግ ስራ ቢሆንም ሚዲያም በምርመራ ጋዜጠኝነት በኩል ይህን ስራ ይሰራል፡፡ ዋናው ጥያቄ የሚሆነው በምርመራ ጋዜጠኝነት በኩል ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን የማጋለጥ ስራ ሲሰራ ምንድነው የሚለየው?የሚለው ነው፡፡ የመጀመሪያው በሚዲያ በኩል ሲሰራ ማህበረሰቡ በቀጥታ ምርመራ ስለሚካሄድበት ተቋም መረጃ ይኖረዋል፡፡ ይህ ማለት ምርመራ በሚደረግበት ተቋም ዙሪያ የሚደረጉ ቃለ-ምልልሶች፣ የተለያዩ ዶክመንቶች ለህዝብ ይፋ ስለሚደረጉ ህዝቡ እውነታውን እንዲረዳ ያደርጋል፡፡ በዚህም ጥናት የተደረገበት ተቋም በሙስናና ብልሹ አሰራር የተዘፈቀ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ተገልጋዩ ማህበረሰብ በራሱ እንዲወስን ዕድል ይሰጣል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከተሰራው የምርመራ ሪፖርት በመነሳት በህግ አካለት ለሚደረግ ምርመራ ደግሞ መንገድ ይከፍታል፡፡ ማለትም የተሰራው የምርመራ ሪፖርት በሚዲያ ከቀረበ በኋላ በፖሊስ ወይም በዐቃቢ-ህግ እንዲመረመር የበለጠ በር የሚከፍት ይሆናል፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ለፖለቲካ አመራሮች መንገድ የሚያሳይ ሲሆን ምንም እንኳን የምርመራ ሪፖርቱ የተሟላ ባይሆንም ምርመራ የተሰራበት ተቋም በሙስናና ብልሹ አሰራር ተዘፍቆ ከተገኘ ተቋሙ ሪፎርም እንደሚያስፈልገው መንገድን ያሳያል፡፡

➢ በዋናነት የምርመራ ጋዜጠኝነት ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው? በተለይም በሀገራችን ደረጃ ለሚለው ጥያቄ ዶ/ር ሳምሶን ማብራሪያ ሲሰጡ እንደተናገሩት፡-

በሀገራችን የምርመራ ጋዜጠኝነትን በተመለከተ ብዙ ተግዳሮቶች አሉት፡፡ በዋናነትና የመጀመሪያ ተግዳሮት ብዬ የማስበው በጋዜጠኛው በራሱ የሚፈጠር ነው፡፡ ይህ ማለት የሙስና ወንጀል እጅግ ውስብስብ እና የትኛውም ሙሰኛ ግለሰብ መረጃዎችን አጥፍቶ እንጂ ጥሎ አይሄድም፡፡ ስለዚህ የምርመራ ዘገባን የሚሰራ ጋዜጠኛ ምን ያህል ነገሮችን ግራ ቀኝ አዙሮ ያያል፣ በምክንያታዊነት ያመዛዝናል እና ምንያህልስ ብልህ ነው? የሚለው ትልቅ ጥያቄ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ የምርመራ ጋዜጠኛ የንስር ዓይን ሊኖረው ይገባል፡፡ አሁን በሀገራችን ያሉ ጋዜጠኞች ይህን በሚሟላት በምርመራ ጋዜጠኝነት በመነሳት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ሊያጋልጡ ይችላሉ የሚለው ትልቁ ጥያቄ ነው፡፡ ምክንያቱም የሙስና ወንጀል ብዙ ሰንሰለቶች ያሉት፣ በትልቅ ሚስጥርና በጥበብ የሚሰራ እንዲሁም የተለያዩ ሀሰተኛ ዶክመንቶች የተዘጋጀበት እና ብዙ ወገኞች የሚሳተፉበት ሲሆን ይህን ሰንሰለት ለመስበር ደግሞ ነገሮችን የማመዛዘንና ገልብጦ የማየት ክህሎት አስፈላጊና አንዱ ተግዳሮት ነው፡፡

ሁለተኛው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የሚታይ ሲሆን ለምሳሌነት የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን የትምህርት ክፍልን ስንመለከት የመርመራ ጋዜጠኝነት/ investigative Journalism የሶስት ክሬዲት ሰዓት አንድ ኮርስ ብቻ ነው የሚሰጠው፡፡ ኢኮኖሚክስ ያልተማረ ጋዜጠኛ የኢኮኖሚ አሻጥሮችን መዘገብ እንደማይችለው ሁሉ አንድ የምርመራ ጋዜጠኛ አንድ ኮርስ ብቻ ተምሮ ወጥቶ የምርመራ ጋዜጠኝነትን በሚገባ በዕውቀት ላይ ተመስረተ ስራ ይሰራል ወይ? የሚለው ትልቁ ጥያቄና ተግዳሮት ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የምናገኘው ተግዳሮት በተቋማት ላይ የሚገኝ ሲሆን ተቋማት ለምርመራ ጋዜጠኝነት/investigative Journalism ምን ያህል ፈቃደኛ፣ ነፃና ገለልተኛ ናቸው ፍላጎቱስ አላቸው ወይ? የሚለው ሌላው ትልቁ ጥያቄ ነው፡፡ እንዲሁም በተቋማት የተሟላ መረጃ አለመገኘት በራሱ ለስራው ትልቁ ተግዳሮት ነው፡፡ አራተኛው ተግዳሮት ደግሞ በመንግስት በኩል የሚታይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ለሚዲያ አካላት መረጃ የመስጠት ግዴታ ቢኖርም አፈፃፀሙ ላይ ግን ተጠያቂነትን የሚያስከትል አይደለም፡፡ የምርመራ ጋዜጠኝነትን የሚደግፍ ራሱን የቻለ በግልፅ የተቀመጠ መመሪያና ደንብ አለመኖሩ ዋነኛው ችግር ነው፡፡

➢ የምርመራ ጋዜጠኞች ምን ዓይነት ስብዕና የተላበሱ መሆን ይገባቸዋል? በሚል ለቀረበው ጥያቄ ዶ/ር ሳምሶን ሲመልሱ፡-

የምርመራ ጋዜጠኝነት በራሱ ብዙ ተግዳሮቶች ያሉበት ሲሆን በጥቂቱ እንኳን ብንመለከት ቃለ-ምልልስ ከማድረግ ጀምሮ የተለያዩ ዶክመንቶችን መመርመር ይጠይቃል፡፡ በዚህም ጋዜጠኛው ትዕግስት እና ብልሃት ሊኖረው የግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱን መረጃዎች በትዕግስት እና በብልሃት ጊዜ ሰጥቶ መመርመር ይገባል፡፡ አንድ የምርመራ ጋዜጠኛ ነገሮችን የመመርመር ክህሎት እና ራሱን በየጊዜው በንባብ ማሳደግም ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም የሙስና ወንጀል ከቀን ወደ ቀን እራሱን የሚቀያይርና ውስብስብ የሆነ ወንጀል ነው፡፡ ሌላው ለሙያው ታማኝ መሆን አለበት፡፡ ይህ ማለት ጋዜጠኛው በራሱ ከሙስና የፀዳ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

➢ በሀገራችን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር የምርመራ ጋዜጠኝነት ያለበትን ደረጃ እንዲሁም የምርመራ ጋዜጠኝነትን እንዲጎለበት ከተለያዩ አካላት ምን ይጠበቃል? ለሚለው ጥያቄያችን ማብራሪያ የሠጡት ዶ/ር ሳምሶን፡-

የምርመራ ጋዜጠኝነት በሀገራችን ገና ጨቅላ የሚባል ደረጃ ላይ እንዳለ ገልፀዋል፡፡ የሚሰሩ የምርመራ ሪፖርቶችም ሙሉ በሙሉ የጋዜጠኝነት መርሆዎችን የተከተሉ አይደሉም ያሉት ደ/ር ሳምሶን በዚህ ረገድ በጣም ብዙ ጉድለቶችን ነቅሶ ማውጣት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

## ቆይታ

የምርመራ ጋዜጠኝነትን እንዴት ነው ማሳደግ የሚቻለው የሚለው? ትልቅ ጥያቄ ነው ያሉት ዶ//ር ሳምሶን ከዚህ አኳያ ከተለያዩ አካላት የሚጠበቁ ነገሮች አሉ ፡፡ ከፍተኛ የትምህረት ተቋማትን በተመለከተ የምርመራ ጋዜጠኝነት (investigative Journalism) በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ማጠናከር አንደኛው ሲሆን የምርመራ ጋዜጠኝነት ራሱን ችሎ በዲፓርትመንት ደረጃ መከፈት ያስፈልጋል፡፡ ሌላው በመንግስት በኩል የምርመራ ጋዜጠኝነትን የሚደግፍ ግልፅ የሆነ መመሪያና ደንብ ወጥቶ ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡ ተቋማት በራሳቸው ደግሞ በራቸውን ለጋዜጠኛው ክፍት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አሁን ያለው ሁኔታን በተመለከተ በሩ ሙሉ በሙሉ ለምርመራ ጋዜጠኝነት ዝግ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ተቋማት የመርመራ ጋዜጠኘነት ለተቋማቸው ጥቅም እንጂ ጉዳት እንደሌለው ሊያዉቁ ይገባል፡፡ የሚዲያ ተቋማትን በተመለከተ ለምርመራ ጋዜጠኝነት ሪፖርት በቂ የሆነ የአየር ሰዓት መስጠት እና ለጋዜጠኞቻቸውም የክህሎት ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ደግሞ የምርመራ ጋዜጠኝነት እንዲጠናከር ስራ መስራት አለበት፡፡ ጋዜጠኞች የምርመራ ጋዜጠኝነትን መስራት እንዳለባቸው በተለይ ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል ጋር ተያይዞ በደንብ በመስራት ኮሚሽኑ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያደርገውን ጥረት እንዲያግዙ ለጋዜጠኞች ስልጠና መስጠት አለበት፡፡ በተጨማሪም ለሚዲያ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሰራርን በተመለከተ ዘገባዎችን አንዲሰሩ አጀንዳ ማስያዝ ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም የምርመራ ጋዜጠኝነትን በማጠናከር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚደረገው ጥረት የሁሉም አካላትን ርብርብ እንደሚጠይቅ ዶ/ር ሳምሶን አስታውቀዋል፡፡

### “የትኛውም ተቋም ይሁን የተቋሙ ኃላፊ ለምርመራ ጋዜጠኝነት በራቸውን ዝግነው ! ”



ዶ/ር ጌታዋ ሞላ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የስልጠና ጥናት ተቋማ ም/ኃላፊ

ሙስና እና የምርመራ ጋዜጠኝነትን ምን ያገናኛቸዋል? ስንል ለዶ/ር ጌታዋ ላቀረብንላቸው ጥያቄ ሲያብራሩ የምርመራ ጋዜጠኝነት በባህሪው ሙስናም ይሁን ብልሹ አሰር ምክንያት ሆን ተብሎ በድብቅ የተሠራን ስራ ከመደበኛው የጋዜጠኝነት ስራ በተለየ መንገድ እና በተለየ አሠራር የተደበቀን ነገር ፈልፍሎ የሚያወጣ ስራ ነው፡፡ ስለዚህ የሙስና ወንጀል ደግሞ በተለየ መንገድ ተደብቆ የሚሰራ ወንጀል ሲሆን የምርመራ ጋዜጠኝነት ደግሞ ይህን በድብቅ የተሠራን ወንጀል ፈልፍሎ የሚያጋልጥ የጋዜጠኝነት የሙያ ዘርፍ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ብሮድካስቲን አማካኝነት የሚተላለፍ ዐይናችን የተባለው የምርመራ ጋዜጠኝነት ስራ ምን ይመስል እንደነበር ሲገልፁ፡-

በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮፖሬት ከ1993ዓ.ም ጀምር እስከ አሁን ድረስ ዐይናችን የተባለ የምርመራ ጋዜጠኝነት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ወጥነት ባይኖረውም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከማጋለጥ አንፃር በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፡፡ በዚሁ ፕሮግራም አማካኝነት ብዙ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲጋለጡ በማድረግ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ እና አጥፊዎችም ለህግ እንዲቀርቡ አድርጓል፡፡ በአሁኑ ወቅት በተቋሙ ውስጥ ከዐይናችን ፕሮግራም በተጨማሪ ብርቱ ወግ የሚል በምርመራ ጋዜጠኝነት ላይ ያተኮረ ከሙስና ጋር እንዲሁም አጠቃላይ ብልሹ አሰራሮችን በማጋለጥ ረገድ የራሱ የሆነ የስራ ክፍል ተቋቁሞለት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በዐይናችን ፕሮግራም ተሰርተው ለውጥ ካመጡ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ውስጥ ሲገልፁ፡-

በዐይናችን ፕሮግራም በጣም በርካታ ስራዎች ተሠርተዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለመጥቀስ ያህል የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በዘውዲቱ ሆስፒታል ላይ ያስጠናውን ጥናት መነሻ በማድረግ የተሰራ ሲሆን በዚህም በሆስፒታሉ ዕድሳት ተደርጎለታል ተብሎ በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ያስነሳና ከፍተኛ የሆነ የሙስና ወንጀል የተፈፀመበት ሲሆን በዚያ ላይም የምርመራ ስራ ተሰርቶ ለህዝብ ይፋ ተደርጓል፡፡

ሌላው የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ድርጅትን የተመለከተ ሲሆን በወቅቱ የነበሩ የስራ ኃላፊዎች በድርጅቱ ስር የነበሩ ቦታዎችን በህገ-ወጥ መንገድ ከመንግስት ዕውቅና ወጪ በሆነ መንገድ ቦታዎችን ለፋብሪካ ጭምር ሸንሽነው በማከራየት ለግል ጥቅም እንደሚያውሉት የተሰራ የምርመራ ፕሮግራም ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም ላይ ተመስርቶ ድርጅቱ ላይ በተሰራ ሪፎርም ስራ ነው የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ድርጅት አሁን ያያዘውን ቁመና ያገኘው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ሰፋፊ ቦታዎች ለብዙ ጊዜ ምንም ዓይነት ልማት ሳይካሄድባቸው ታጥረው መቀመጣቸውን በተመለከተ በወቅቱ መልስ ማግኘት ባይችሉም ከሁለት ጊዜ በላይ ፕሮግራም ተሰርቶባቸዋል፡፡

በተጨማሪም አዲስ አባባ ውስጥ ሻሌ የተባለ መናፈሻ የሚገኝ ሲሆን ከ1969 አካባቢ የተቋቋሙ የመናፈሻ ቦታዎች ሲሆኑ ለረጅም ጊዜያት ማለትም ከ 40 እና 30 ዓመት በላይ ባለቤት ያልነበራቸው ሲሆን በዚህም የመዝናኛ ኃላፊዎቹ ብቻ ለግል ጥቅም ሲያውሉዋቸው ቆይተው ነበር፡፡ ይህን የምርመራ ስራ መነሻ በማድረግ አዲስ አበባ ውስጥ በርካታ ስራዎች ተሰርቶ ነበር፡፡ አሁን ያለው የሸማቾች ማህበር የተቋቋመው ከዚያ የመርመራ ስራ በኋላ ነው፡፡ በተጨማሪም ከአዲስ አበባ ውጪ በሆሳዕና እና ሻሸመኔ እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በርካታ የምርመራ ስራዎቸ ተሰርተዋል፡፡

ዶ/ር ጌታዋ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ተግባራዊ ለማድረግ የተሄደበትን ርቀት ሲገልፁ፡-

በመጀመሪያ የምርመራ ጋዜጠኝነት ለመስራት እጅግ አሰቸጋሪ ሲሆን በተለይ ደግሞ አጠቃላይ የምርመራ ጋዜጠኝነት ስራ በአሉታዊ መንገድ ስለሚታይ ውስጣዊም ውጫዊም ጫናዎች አሁን ድረስ አሉበት፡፡ የመርመራ ጋዜጠኝነትን ለመስራት መታሰር፣ መደብደብ፣ መንገላታት እንዲሁም የተሰራ ፕሮግራም አንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡ የምርመራ ጋዜጠኝነትን በሀገራችን ለመስራት እጅግ ከባድ ነው፤ ነገር ግን ከተሰራበት ጥቅሙ ትልቅ ነው፡፡ በመልማት ላይ ባሉ ሀገር ውስጥ ከልማት ጋር ተያይዞ የሚመጣ የሙስና ወንጀል እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ውስጥ ደግሞ የብልሹ አሰራሮች ስለሚኖሩ የምርመራ ጋዜጠኝነት በጣም ጠቃሚና ወሳኝ ቢሆንም በሀገራችን ግን ብዙ ፈተናዎች አሉበት፡፡

ተቋማት ለምርመራ ጋዜጠኝነት ያላቸው አመለካከትን በተመለከተ እንደ ዶ/ር ጌታዋ ገለፃ፡-

የምርመራ ጋዜጠኝነት ሙያ በድብቅ የሚሰራ ስራ አይደለም፡፡ ሊሰራ የተፈለገውን ስራ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለተቋማት ማብራሪያ ይሰጣል እንግዲህ ገና ከዚህ ጀምሮ ነው ተቋማት በራቸውን የሚዘጉት፡፡ የትኛውም ተቋም ይሁን የተቋሙ ኃላፊ ለምርመራ ጋዜጠኝነት በራቸውን አይከፍቱም ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ በተለይ ከለውጡ በፊት የነበረው ችግር ምርመራውን ከፖለቲካ ጋር ማያያዝ ነበር፡፡ ሌላው ጋዜጠኛውን በተመለከተ ሲሆን የምርመራ ጋዜጠኝነት ምንጊዜም ቢሆን የመረጃ አሠባሠብ ስልትን ይጠይቃል፡፡ ይህ ማለት የሙስና መረጃ እንዲሁ ስጡኝ ተብሎ የሚገኝ አይደለም የጋዜጠኛውን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድንና የመረጃ አሠባሠብ ስልትን ይጠይቃል፡፡ በዚህ መሰረት ነው የምርመራ ጋዜጠኝነት የሚከናወነው፡፡ በተጨማሪም የተቋማት ኃላፊዎች መረጃ እንዲሰጡ የሚያስገድድ ህግ አለመኖሩ በራሱ ትልቅ ችግር ነው፡፡

ዶ/ር ጌታዋ የምርመራ ጋዜጠኝነት ሙስናና ብልሹ አሰራርን በየተቋሟቱ ከመከላከል አንፃር ያለውን ፋይዳ ሲያስረዱ እንደገለፁት፡-

በአጭሩ የምርመራ ጋዜጠኝነት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር በተቋማት ላይ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ያረጋግጣል፡፡ ሌላው የተቋሙ ተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ እንዲያደርስ ይረዳዋል፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራር ከሌለበት የህዝብ ሀብትና ንብረት ለታለመለት ዓላማ ይውላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በየተቋማት የሚገኙ የህዝብ ግኑኝነት ባለሙያዎች ምርመራው እንዳይካሄድ በማድረግ ረገድ ትልቅ ችግር ፈጣሪዎች ናቸው በማለት ይገልፃሉ፡፡

ሙስናና ብልሹ አሰራርን በምርመራ ጋዜጠኝነት ለመከላከል ይረዳ ዘንድ ከተለያዩ አካላት ምን ይጠበቃል ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ ዶ/ር ጌታዋ መልስ ሲሰጡ እንደገለፁት፡

በመጀመሪያ የምርመራ ጋዜጠኝነትን በተመለከተ አጠቃላይ ፋይዳውን በመረዳት ለስራው ጥሩ አመለካከት ኖሮት ስራው እንዲሰራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ የሚያተኩሩ ተቋማት አንድ ላይ ቅንጅት መስርተው መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ከለውጡ በፊት ብዙ ስራዎች ተሰርተው ሳይተላለፉ ቀርተዋል፡፡ ያኔ በወቅቱ እርምጃ ቢወሰድባቸው ኖሮ አሁን የሚታየውን ግዙፍ ችግር ይቀንሱ ነበር፡፡ የምርመራ ጋዜጠኝነት ስራ የሚሰሩ የሚዲያ ተቋማትን ማበረታታትና መደገፍ አስፈላጊ ነው፡፡



# ሳይቃጠል በቅጠል

## የፍርድ ቤቶች የሙስና ስጋት ዳሰሳ



ሙስና ዘላቂ ልማትና የሕግ የበላይነትን አደጋ ላይ በመጣል፣ የዲሞክራሲ ተቋማትና የሥነምግባር እሴቶችን በማመንመን በማህበረሰቡ ላይ ከሚያስከትለዉ ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ጎን ለጎን የሚያሳድረዉ የሠላምና አለመረጋጋት ስጋትና አደጋ አሳሳቢነት ቀላል ቦታ የሚሰጠው አይደለም፡፡

ችግሩ በአንድ አካባቢ ወይም አገር ብቻ ሳይወሰን በዓለም ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ከባቢያዊ ሂደት ላይ ጭምር ጉዳት የሚያደርስ ከመሆኑ ባሻገር የደረሰውን ጉዳት ለመጠገን የሚደረገው ጥረት አብዛኛውን ጊዜ ስኬታማ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ጉዳቱን አስቀድሞ መከላከል ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

የሙስና መከላከል ስራ ከወንጀሉ ልዩ ባህሪ አኳያ በበቂ መረጃ ላይ ተመስርተዉ በሚከናወኑ የተለያዩ የጥናት ሥራዎች ላይ የሚደገፍ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥም የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥንት አንዱ ነዉ፡፡ይህ ጥናት በዋናነት የአንድን ዘርፍ፣ተቋም ወይም አሰራር ለሙስና ድርጊቶች ያለዉን ስጋት ደረጃ የሚያመላክት ሲሆን ለዚህም በዋናነት ሁለት የመመዘኛ መስፈርቶችን የሙስና መከሰት እድልን እና የሙስና መከሰት የተጽእኖ መጠንን ይጠቀማል፡፡

በነዚህ መመዘኛዎች በሚደረግ ልኬት የሙስና ደረጃዎችን ከፍተኛ ሥጋት፣መካከለኛ ስጋትና ዝቅተኛ ስጋት ብሎ በመከፋፈልና ስጋቶችን ለመቅረፍ የሚረዳ ምክረሃሳብና የስጋት መቆጣጠሪያ ስትራቴጂ በመንደፍ በደረጃ ቅደም ተከተላቸዉ መሰረት ችግሮችን ለመፍታት ወይም ለመከላከልት የሚያስችል የጥናት ዘዴ ነዉ፡፡ይህ አሰራር በዋናነት በእዉር ድንብር የሚደረገን ጉዞ በመገደብ በአንድ ዘርፍ፣ተቋም ወይም አሰራር በቅድሚያ የሙስና መከላከል ስራዉ ያስፈልጋል?ካስፈለገ የተተኳሪነት/አጣዳፊነት ደረጃዉ ምን ያህል ነዉ?ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ ከሆነ በየትኛዉ መንገድ ቢፈታ ይበልጥ ተመራጭ ይሆናል?የሚሉ ቁልፍ ጥያቄዎችን በመመለስ ኢላማዉን የሚመታና ወጪ ቆጣቢ የሙስና መከላከል ስልት በመንደፍ አጠቃላ የፀረ ሙስና ትግሉ «ከብት ባልዋለበት...» እንዳይሆን ከማገዙ ባሻገር የሚደረገዉን ጥረት ዉጤታማነት ለማሳደግ በከፍተኛ ሁኔት የሚረዳ ይሆናል፡፡

የፍትህ ዘርፍ ካለዉ ልዩ ባህሪ በመነጨ ለሙስና ተጋላጭ ዘርፍ ሲሆን ሙስና ቢስፋፋ አጠቃላይ የዜጎች የመጨረሻ ዋስትና እንደመሆኑ ከሚፈጥረዉ ተስፋ መቁረጥና ማህበራዊ ቀዉስ አንጻር ተተኳሪ ዘርፍ ሆኖ የሚወሰድና በሙስና መከላከል ስራ ዉስጥም ቅድሚ ከሚሰጣቸዉ ዘርፎች ተርታ የሚሰለፍ ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር በሃገራችን ራሱን ችሎ በፍርድቤቶች ዙሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት የተካሄደ ሲሆን በዚህም የሥጋት አካባቢዎችን በመለየት ምክረሃሳቦችን ለማመላከት ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በተመረጡ ፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ ትኩረት የሚሰጠው በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት በዝርዝር መለየት፤ የሙስና ምክንያቶችን መተንተን፤የሙስና ስጋት መገምገም፤ እና የሙስና መከላከያ ምክረሀሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ፌዴራል ከፌተኛ ፍርድ ቤት፣ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ፤ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ በስሩ ያሉ ሶስት ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና ሶስት ወረዳ ፍርድ ቤቶች፤ እንዱሁም በደቡብ ክል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስሩ ያለ ሶስት ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና ሶስት ወረዳ ፍርድ ቤቶች ነዉ ፡፡

የጥናቱ አጠቃላይ አላማ በፍ/ቤቶች የሚታዩ የሙስና ስጋቶችን ማጥናት ሲሆን አላማዉን ለማሳካት በዋናነት የጥናቱ ግብዓት የሚሆን መረጃ በቃለመጠይቅ፤ በጽሁፍ መጠይቅና ከሰነድ ማስረጃዎች ተገኝቷሌ፡ ፡ በዚህም መሰረት 36 ግለሰቦች በሁለም የጥናት ቦታዎች መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቅን በመሙላት ባጠቃላይ 354 መጠይቆች በሁለም የጥናት ቦታዎች እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የሃሳብ ማጎልበት (brainstorm)፤ እና የጥናቱ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ሰነዶች እና መረጃዎች ተካተዋል፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በፍርድ ቤቶች ዉስጥ የፍትህ ተደራሽነትና ተገማችነት ችግር፤ የፍትህ መዘግየት፤ በአድሎ ትክክለኛና ህጋዊ ውሳኔ አለመስጠት፤ ህግን ተከትሎ ያለመስራት ፤ በወገንተኝነትና በዘመድ አዝማድ መስራትና መወሰን፤ ያልተገባ ጥቅም በማግኘት መስራት ፤ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት፤ ባለጉዳይን ማጉላላት፤ የዳኝነት ነጻነት ችግር፤መዝገብ መጥፋት፤ የፍርድ አፈጻጸም መዘግየት፤ግልጽነት የጎደለዉ የዳኞች ምልመላ ፤መረጣ ፤ሹመትና እድገት፤ህግን ያልተከተለ የሰው ሃይል ቅጥር፤ዝውውር፤ የደረጃ እድገት፤የንብረት መባከንና ያልተገባ የግዥ አሰራር የሚታዩ የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች ናቸው፡፡

በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ የሚታየዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በተናጠል ሢታይ የሚያሳየዉ ዉጤት የዋስትና መብትን ያላግባብ መከልከል ወይም መፍቀዴ ፤የወንጀል ተከሳሽን ያላግበባ ጥፋተኛ ማለት ወይም ነጻ መልቀቅ ፤ቅጣት መጨመር ወይም መቀነሰ ጉዳዮች ላይ የስጋት ደረጃ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በፍርድ አፈጻጸም አገልግሌት በኩል በአማካኝ ሲታይ ሙስና የመከሰት እድሉ ከፍተኛ ፤ የሙስና ተጽእኖ ከፍተኛ ፤ስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ፡፡ የዳኞች አስተዲደርን በተመለከተ በአማካኝ ሲታይ የስጋት ደረጃዉ መካከለኛ ነዉ ፡፡ በሬጂስትራር ዳይሬክቶሬት በኩል በአማካኝ ሲታይ የስጋቱ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ፡፡ በሰዉ ሀብት አስተዳደር እና በግዥ አስተዳደር በኩል የስጋቱ ደረጃ ዝቅተኛ ነዉ፡፡

ጥናቱ እንዳመላከተዉ የሙስና ገፊ ምክንያቶቹ በጥቅሉ ሲታዩ የሚያያዘው የዳኞች ምልመላ ፤መረጣና ሹመት በብሄር ተዋጽኦ ፤ በፖለቲካ ዉሳኔ እንጂ በጥናት ላይ ያልተመሰረተ ከመሆኑ፤ ግልጽነት እና ተጠያቂነት የሰፈነበት ስርአት ያለመኖሩ በዚህም ምክንያት በተመደቡበት ሀላፊነት ብቃት ማነስ ፤ አቅምን የማጎልበት ፍላጎት ማጣት፤በአቋራጭ የመክበር ዝንባሌ መኖር፤የቁጥጥር ስርአት እና ተጠያቂነት መላላት ፤በተጨማሪም በቂ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም ያለማግኘት፣ ምቹ የስራ ሁኔታን ያለመፈጠር ጎልተዉ የወጡ ናቸዉ፡፡በጥቅሉ ሲታይ በፍርድ ቤት የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ተጽኖዎች ቁሳዊ ያልሆነው ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ ፍትህ እንዲዛባ ማድረጉ ፤የፍትህ ስርአቱ አመኔታ መጥፋት ፤ የፍትህ ተገማችነት መጥፋት ፤ የባለጉዳይ መጉላላት፤ተስፋ መቁረጥ፤ ዜጋዉ በሀገሩ ላይ ባይተዋር እንዱሆን እና መንግስት ላይ አመኔታ እንዳይኖረው ማድረግ ተጠቃሾች ናቹዉ ፡፡

የዳሰሳ ጥናቱ ይህንን ችግር ከመቅረፍ አንጻር ጠንካራ አመራርና አሰራርን መዘርጋት፤የዳኞች ምልመላን፣ መረጣንና ሹመትን የሙያ ብቃትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፤ የዳኞች ነጻነትንና ተጠያቂነትን ስርአት ማስፈን ፤ክትትልና ድጋፍ ማጠናከር የሙያ ግምገማ ማድረግ ፤ ምቹ የስራ ሁኔታን መፍጠር፤የፍትህ ስርአቱ ተገማች የሚሆንበትን የአሰራር ስርአት መዘርጋትና ማሳደግ ተገቢ መሆኑን ያመላከተ ሲሆን በተለይም ግልጸኝነት እና ተጠያቂነትን ማስፈን ችሎቶች ለህዝብ ግልጽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ህብረተሰቡን በፍርድ ቤት አሰራር ማወያየትና (ንቃተ-ህግ) አስተያየቶችን መሰብሰብ አስፈላጊና የዘርፉን ስጋት ለማቃለለ እንደመፍተሄ ሊወሰድ የሚገባዉ መሆኑን አመላክቷል፡፡

➢ ማስታወሻ ከፍርድ ቤቶች የሙስና ዳሰሳ ጥናት የተወሰደ

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

## የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች

ባለፈው ወር የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 በአጭሩ ለማስተዋወቅ የሚረዳውን የመጀመሪያውን ክፍል ማስነበባችን የሚታወስ ነው፡፡ በዚያ አጭር ጽሁፍ ውስጥ በስልጣን አላግባብ መጠቀም፣ ጉቦ መቀበል፣ የማይገባ ጥቅም መቀበል፣ አስታራቂ ሽማግሌዎች እና ሌሎች ሰዎች የሚፈጽሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል፣ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅትን ሥራ በማያመች አኳኋን መምራት፣ አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ፣ በሥራ ተግባር የሚፈጸም የመውሰድና የመሠወር ተግባር እና በስልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ የሚሉትን ርዕሰ ጉዳዮች ለማስተዋወቅ ተሞክሯል፡፡ በዛሬው ጽሁፍ ደግሞ በአዋጁ ላይ የተካተቱትን ቀሪ ርዕሰ ጉዳዮች በአጭሩ ለማስተዋወቅ በሚከተለው መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

### 10. ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራው ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው (ባለጉዳይ) በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ወይም ሌላ ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ከሕግ፣ ከደንብ እና ከመመሪያ ወይም ከተለመደው አሠራር ውጪ ያለበቂ ምክንያት ያልወሰነ፣ ያዘገየ ወይም ባለጉዳይን ያጉላላ እንደሆነ ከህግ ፊት ቀርቦ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 11. ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማጽደቅ

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ሆን ብሎ ብቁ ላልሆነ ወይም በሕግ ሊሰጠው ለማይገባ ማናቸውንም ሰው የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሠጠ ወይም ያጸደቀ እንደሆነ ያለአግባብ ፈቃድ መስጠት ወይም ማጽደቅ በሚል የሙስና ወንጀል አንቀጽ ክስ ሊመሰረትበት እና ጥፋተኛ ሆኖም ከተገኘ እስከ አሥር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እና እስከ 30 ሺህ ብር የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊጣልበት ይችላል፡፡


በዚህ አንቀጽ ውስጥ ለማይገባው ሰው የመንጃ ፍቃድ፣ የትምህርት ደረጃና የጤና ማረጋገጫ እንዲሁም የተሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ያለአግባብ መስጠትንም ይካተታል፡፡

### 12. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነና የነበረ ሰው የኑሮ ደረጃው በሕጋዊ መንገድ ከሚያገኘው ገቢ የበለጠ እንዲሆን የዚህ ዓይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ያለው ንብረት ወይም ገንዘብ እንዴት እጁ ሊገባ እንደቻለ በበቂ ማስረጃ ማስረዳት እስካልቻለ ድረስ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በመያዙ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 13. የሥራ ምስጢርን መግለጽ


ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሌላ ሰውን ጥቅምና መብት ለመጉዳት በሥራው ምክንያት ያወቀውን ወይም በሚስጥር እንዲጠብቅ የታዘዘውን መረጃ ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራውን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላም እንኳ ቢሆን ከገለጸ ወይም ካስተላለፈ ምስጢሩን ባለመጠበቁ ህግ ፊት እንዲቀርብ ይገደዳል፡፡






### 14. መንግስታዊ ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል

ማንኛውም ሰው የሌላ ሰውን ጥቅም ወይም መብት ለመጉዳት ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት አንድ ሰነድ የመንግስት፣ የሕዝባዊ ድርጅት አስመስሎ ያዘጋጀ፣ በመንግስት፣ በሕዝባዊ ድርጅት መዝገብ ጽሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ጽሁፍ በመደለዝ የለወጠ እንደሆነ ሙስና ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ አቃቤ ህጉ ችሎት ያቀርበዋል፡፡



### 15. መንግስታዊ ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ

ማንኛውም ሰው የሌላ ሰውን ጥቅም ወይም መብት ለመጉዳት ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በሕዝባዊ ድርጀት ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አስር አመት የሚደርስ እስር ይጠብቀዋል፡፡ ከአስር ሺህ እስከ ሰባ ሺህ ብርም መቀጮ ይጣልበታል፡፡

### 16. ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት

ማንኛውም ሰው አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ




ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ ከቀላል ቅጣት እስከ ሰባት አመት የሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ይከሰሳል፡፡

### 17. ዋጋ ያለው ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት

ማንኛውም ሰው ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ለመንግስት ሠራተኛ ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋራ ግንኙነት ላለው ለማንኛውም ሌላ ሰው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማንኛውንም ዋጋ ያለው ነገር ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ከሙስና ወንጀል ፈፃሚዎች አንዱ ነው፡፡

### 18. ማቀባበል

ማንኛውም ሰው ለራሱ ጥቅም ባያገኝም እንኳን ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለው ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ አይነት ጥቅም ከሌላ ሰው የተቀበለ እንደሆነም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ ማቀባበል የሚከለክለውን አንቀጽ እንደሻረ ይቆጠርና በሕግ ይጠየቃል፡፡

### 19. በሌለው ስልጣን መጠቀም

ከመንግስት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው የታገደ፣ የተዟወረ፣ የተሻረ፣ የተወገደ፣ ስልጣን ኃላፊነቱን የተወ ማንኛውም ሰው ሠራተኛ ሳይሆን ሠራተኛ መስሎ በመቅረብ ይህን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ስጦታ ከሌላ ሰው መጠየቅ መቀበል በሙስና ወንጀል ህጉ መሰረት ያስቀጣል፡፡

### 20. በግል ተሰሚነት መነገድ

የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ያልሆነ ሰው ያለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ እጅ መንሻ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ፣ የተስፋ ቃል የሰጠ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል፡፡

### 21. በምርጫ ወቅት የሚሰጥ መደለያ

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለውን ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብም ይሁን ማናቸውንም ሌላ ዓይንት ጥቅም የሰጠ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ በእስር ቅጣት ይቀጣል፡፡

የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ማንኛውም ሰው በዚሁ በመብቱ እንዲጠቀምበት በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም ሳይጠቀምበት እንዲቀር ገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ ማንኛውም ሰው የሙስና ወንጀል ፈጽሟል፡፡

### 22. ከባድ የእምነት ማጉደል

የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት የሆነውን እና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ የወሰደ፣ ያስወሰደ የሰወረ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ በከባድ የእምነት ማጉደል ይጠየቃል፡፡

### 23. ከባድ አታላይነት

የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር የራሱን ማንነት በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም በማድረግም ሆነ ባለማድረግም ሌላውን ሰው በማታለል የተታለለው ሰው የራሱን ወይም የሌላውን ሰው የንብረት ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት እንዲፈጸም ያደረገ እንደሆነ ከሙስና ወንጀሎች አንዱን ፈጽመዋል፡፡

### 24. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ የህጉ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ተግባሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ወንጀል ክስ ይቀርባል፡፡

(የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን)

# ኪነ-ጥበብ



*ሥነምግባር ግጥም*

## ዕዳ አልባ የሆንከው

ሽማኔው ሰርቷል ተጠቦ ይለበስ ሸማ ከነ ትጥቁ፣
እንዶድ ሳሙና አለቀ እንጂ ጥጡ የጠፋው ከፍልቁ፡፡
የጥንት መነሻህ፣
ያንተ መሰረትህ፣
ሳያውቅ ያሳወቀህ፡፡
የሌለውን ሰጥቶ፣
ወዛም ያደረገህ ለራሱ ገርጥቶ፡፡
እርሱ ከምድር ምድር አፈር እየገፋ፣
በአየር ብረር ያለህ እንድትሆነው ተስፋ፡፡
በአንተ አለማስተዋል ወይ ግዴለሽነት፣
አሊያም ኋላን መርሳት ማን አለብኝነት፣
ይባሱን ስግብግብ አልጠግብባይነት፡፡
ወገን ውሃ ጠማው፣
የእግዜሩ ስጦታ እጅጉን ቢርቀው፣
ደረቅ አሸተተ ከልቡ ላይ ሲያንቀው፡፡
አንተ አቅም ማጣትህ ምንም አልነበረም፣
ከሌለህ የለህም በአንተ አይዘከርም፡፡
ባዕዳን የቸሩትን የሰጡትን ንዋይ፣
ምን አለበት ባታይ?
ምን ነበር ጉድጓዱን ብትቆፍር አርቀህ፣
መና ከፈለቀ ለአንተ ለወገንህ፡፡
የውሃ ጥም ነገር ጊዜ አይሰጥምና፣
በአንተ ተስፋ መጣል ቢሆንበት መና፡፡
ረኸርም ተጉዞ ከአውሬ ጋር ቢጠጣ፣
አተረፈ ጣጣ፡፡
የበሽታ ጎሬ የተውሳክ መደብር፣
ሆነ የርሱ ነገር፡፡
በአንተ አለማስተዋል ወይ ግዴለሽነት፣
አሊያም ኋላን መርሳት ማን አለብኝነት፣
ይባሱን ስግብግብ አልጠግብባይነት፡፡
መንገድ ሰሪ ብትሆን እድሉን አግኝተህ፣
ከገንዘብ ቦጭቀህ፣
ከጊዜ ጎትተህ፣
ሰራሁ ብትል እንኳን እንቶ ፈንቶ አድርገህ፣
የጥንት መነሻህ፣
ያንተ መሰረትህ ፣
አንት በረቀቅህበት በዛሬው ዘመንህ፡፡
ህሙም በቃሬዛ እየተሸከመ፣
በማረፊያው ሰአት እጅጉን ደከመ፡፡
መዳን እየቻለ ሳይደርስ እያረፈ፣
መንገድ በማጣቱ ስንቱ ተቀጠፈ፣
ስንቷስ ወላድ ቀረች ሽሏም ጨነገፈ፣
በዚህ ሁነት ማለፍ የተንገፈገፈ፣
በሚወዳት ምድሩ መኖር ተፀየፈ፡፡
እልፍ ሲሉ እልፍ የሚል ብሂል ይዞ፣
ትውልድ ውሃ በላው ቀለብ ሆነ ለአዞ፡፡
በአንተ አለማስተዋል ወይ ግዴለሽነት፣
አሊያም ኋላን መርሳት ማን አለብኝነት፣
ይባሱን ስግብግብ አልጠግብባይነት፡፡
ይህን ውጣ ውረድ በጥንካሬ አልፎ፣
አንተ ባለሙያ በሆንክበት ጣቢያ ሲደርስ ተደግፎ፡፡
ማረፊያ አልጋ የታል፣
ዕድሉ ተሸጦ ዋጋው ኪስህ ገብቷል፡፡

በስንት ደጅ ጥናት በስንት እግዚዮታ፣
ማረፊያውን ሲያገኝ ያ ሚስኪን ከርታታ፡፡
መድሃኒት ከወዴት፣
ስንት አሳር አለበት፡፡
መቀነቷን ፈታ ጥሪቷን አሟጣ፣
አሊያም ደጅ ፀንታ ከዚያም ከዚህ ቧጣ፡፡
ሀገር ያስመጣችው ለዜጎቿ ድህነት፣
ለገበያ ውሏል በአንተ ከሃዲነት፣
በአንተ አለማስተዋል ወይ ግዴለሽነት፣
አሊያም ኋላን መርሳት ማን አለብኝነት፣
ይባሱን ስግብግብ አልጠግብባይነት፡፡
በእጅህ ያለን መክሊት አትርፈህ ባትመልስ፣
ተማሪ ቤት ሊሆን ባጥልላቸው ዳስ፡፡
የአንተ ተከታዮች እህት ወንድሞችህ፣
ከዕውቀት ጨዋ ሆኑ እንደ እናት አባትህ፡፡
ዕውቀት ቀመሶቹ መግፋት ያልታደሉት፣
ጠብ አልል ቢላቸው አልቋቋም ቢሉት፣
ስደትን በመምረጥ ሆኑ የጅብ እራት፣
በአንተ አለማስተዋል ወይ ግዴለሽነት፣
አሊያም ኋላን መርሳት ማን አለብኝነት፣
ይባሱን ስግብግብ አልጠግብባይነት፡፡
እንጂ ኢትዮጲያ እንደ ሀገር ድሀ አልነበረችም፣
ህዝቦቿ እድለ ቢስ እርጉምም አይደሉም፡፡
አይንህ ባያማትር የማይገባውን፣
እጅህ ባይቀበል ያንተ ያልሆነውን፡፡
በንዋይ ባትለውጥ የወገንህን ዕድል፣
ልበልፀግ በአቋራጭ ልሹለክ በአጭር ባትል፡፡
ህሊናህ ሲወቅስህ ጆሮ ብትሰጠው፣
በደም ወዝህ ብትኖር ልክህን ብታውቀው፡፡
ለእኔ ብቻ ባይኖር እይታ ቢሰፋ፣
ሰርዶ አይብቀል ባይል ሰው እርሱ ከጠፋ፣
እጁን ቢሰበስብ ሆዱን ባያሰፋ፣
እንደ ሀገር ቢታሰብ ነግ በእኔ ባይጠፋ፣
ከዛሬው በባሰ ነገአችን ባልከፋ፡፡
አየህ አይደለም ጃል ?
በአንተ አለማስተዋል ወይ ግዴለሽነት፣
አሊያም ኋላን መርሳት ማን አለብኝነት፣
ይባሱን ስግብግብ አልጠግብባይነት፡፡
የተቀበለችህ የእትብትህ ምድር ፣
ግባተ መሬትህ ኋላም የአፅምህ ክብር፡፡
ያች ፊተኛይቱ፣
ከኋላ እንደቀረች ካልበለፀጉቱ፡፡
አየህ አይደለም ጃል ?
አሁን አላፊ አልፏል፣
ቀጣይ እንማማል፡፡
በተሰጠህ መክሊት ባለህበት ቦታ፣
ውሎ አዳርህ ይሁን ከሃቅ ገበታ፣
ደግሞም ለወገንህ ይኸው ነው ውለታ፣
የበኩልህን አርገህ በአንተ ልክ ችሎታ፣
ሀገርህን ማሰለፍ ከሃያላን ተርታ፣
መኮነን መፀየፍ የጥቅምን ሰንሰለት የሙስናን ካርታ ፡፡
አዎ ያኔ ነው ዕዳ አልባ የሆንከው የመለስክ ውለታ!!!!!!



# መልካም ዜጋ

## ሙሰናና ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል የባለድርሻ አካላት ሚና ወሳኝ ነው።

ሙስና በራሱ ወንጀል ከመሆኑም አልፎ ሌሎች ወንጀሎች እንዲበራከቱ በማድረግ የዜጎችን ሰላም፤ ፀጥታና ደህንነትን ያቃውሳል፡፡ በሀገር ሀብት፣ በዜጎች ነጻነትና በመንግስት መረጋጋት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ይህንን ዘርፈ-ብዙ የሙስና ችግሮችን ለመከላከል ታዲያ የሁሉንም ህብረተሰብ ክፍል ርብርብ ይጠይቃል፡፡ ሁሉም አካላት በጋራ፣ በግለሰብ እንዲሁም እንደ ተቋም ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል ከሙስና የጸዳ፣ በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጸ ትውልድን የመፍጠር አላማ ለማሳካት አገራዊ ግዴታን እንዲወጣ ይጠበቃል፡፡

ከዚህ አኳያ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ተቋማት ደረጃ የተጀመሩ አበራታች የፀረ-ሙስና ትግሎች ይበል የሚያስብሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት የመልካም ሥነ-ምግባር አርአያ ከመሆን ጀምሮ የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶች በአገርና ህዝብ ላይ በሚፈጥሩ ችግሮች ዙሪያ ማህበረሰቡን ለማንቃትና ለማስተማር ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ አካላት በግለሰብም ሆነ በተቋም ደረጃ የሙስና ወንጀሎችን በማጋለጥም ሆነ በመጠቆም ረገድ አስፈላጊዉን የዜግነት ግዴታ በማበርከት ሲንቀሳቀሱ የቆዩ ናቸዉ፡፡

በፀረ-ሙስና ትግሉ ዙሪያ በተሻለ ሁኔታ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ግለሰቦችና ተቋማት በፀረ-ሙስና ትግሉ ሂደት ውስጥ ቀላል የማይባል የጉልበት፣ የጊዜ እና የሀብት አስተዋጽኦ ከማበርከታቸው በተጨማሪ ከፍተኛ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጥቃቶችን ተቋቁመው እስከ ህይወት መስዋዕትነት ለሚጠይቅ የፀረ-ሙስና ትግል በፅናትና በቁርጠኝነት በመዝለቅ የሚጠበቅባቸዉን የዜግነት ግዴታ ተወጥተዋል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንም እነዚህን አካላት በተለያዩ መንገዶች በመለየት ለመጀመሪያ ጊዜ እውቅና እንዲሰጣቸው አድርጓል፡፡ ኮሚሽኑ የ2012 ዓ.ም ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በዓል አከባበርን ምክንያት በማድረግ በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ በርካታ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ካሉ ግለሰቦች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ መገናኛ ብዙኃን፣ ት/ቤቶች እና ማህበራት መካከል ጥቂቶቹን በመለየት በኮሚሽኑ አሠራር የመጀመሪያ የሆነውን የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሽልማት እውቅና አበርክቷል፡፡ በፀረ-ሙስና ትግሉ የጎላ ድርሻ ላበረከቱ ግለሰቦች እውቅና ለመስጠት ኮሚሽኑ ባደረገው ጥሪና በ2011 ዓ.ም በተሰበሰቡ መረጃዎች ተመዝነው እውቅና የተሰጣቸውን የዘጠኝ ግለሰቦችን አስተዋጽኦ "በመልካም ዜጋ" አምዳችን ላይ በአጭሩ ቃኝተናል፡፡




ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል ለዜግነት ግዴታ እስከ ህይወት መስዋዕትነት ከከፈሉ ግለሰቦች መካከል አቶ መሀመድ አሚን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አቶ መሀመድ በጉምሩክ ኮሚሽን ዉስጥ በተሰማሩበት ቁልፍ የሆነ የሥራ መስክ ከፍተኛ የሆነ ፅናትና ቁርጠኝነትን በተላበሰ መልኩ ኃላፊነታቸዉን የተወጡ መልካም ዜጋ ነበሩ፡፡ አቶ መሀመድ በህገ-ወጦች የሚቀርቡላቸዉ መደለያዎች ሳያጓጓቸው በተመደቡበት የሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ያቤሎ መቆጣጠሪያ ጣቢያ በፅናትና በጠንካራ የሥራ ሥነ-ምግባር ህዝቡንና መንግስትን አገልግለዋል፡፡ ይሁንና ግለሰቡ ኮንትሮባንድን በመከላከል ተግባር ላይ ተሰማርተዉ ባሉበት ሐምሌ 10 ቀን 2011 ዓ.ም በህገ-ወጥ የኮንትሮባንድ አዘዋዋሪዎች/ኮንትሮባንዲስቶች ተሽከርካሪ ሆን ተብሎ ተገጭተው ህይወታቸዉ አልፏል፡፡ መልካም ዜጋ ተግባሩና ዝናው ከመቃብር በላይ ይውላል እንደሚባለው አቶ መሀመድ የሰሩት ጀብዱ ተግባር በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ ለዘላለም ሲታወስ ይኖራል፡፡ አቶ መሀመድ በዚህ የህይወት መስዋዕትነት ላስከፈለው ጽናትና ቁርጠኝነት በአንደኛዉ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሽልማት እውቅና በቅተዋል፡፡ በወቅቱም እሳቸው በህይወት ኖረው የእውቅና ሽልማታቸውን ባይረከቡም ባለቤታቸው ተገኝተው ሽልማቱን በመቀበል ተጨማሪ የሥራ ታታሪነታቸውን በታዳሚዎች ፊት መስክረዋል፡፡



ሌሎቹ የሙስና ወንጀልን በማጋለጥ እውቅና ከተሰጣቸው ግለሰቦች መካከል አቶ ቴዎድሮስ አሰገህኝ እና ወ/ሮ አልታየ ገብረየስ ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በሚሰሩበት በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በተፈፀመ የታክስ ማጭበርበር በድምሩ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ በሙሰኞች እንዳይመዘበር ለመታደግ ጥቆማ አቅርበዋል፡፡ በእነሱ ጥቆማ መሰረት ከ2.6 ሚሊዮን ብር በላይ ለመንግስት ተመላሽ እንዲሆን ተወስኗል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በወንጀሉ ድርጊት የተጠረጠሩ ሰዎች በታክስ ማጭበርበር ወንጀል ህግ እንዲጠየቁ የተደረገ ሲሆን 6 ሰዎች ደግሞ ተጭበርብሯል የተባለውን ገንዘብ ለመንግስት እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ እና ወ/ሮ አልታየ ጥቆማ ከማቅረብ ባሻገር በፍርድ ሂደቱ ወቅት የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነው በመቅረብ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ተወጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የ3.5 ቢሊዮን ብር ታክስ ማጭበርበር ጥቆማ አቅርበው ጉዳዩ በምርመራ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ ትጉ የፀረ-ሙስና ታጋዮች በጉዳዩ ዙሪያ ኦዲተሮች በሚያካሂዱት የማጣራት ሥራ ላይም በአስረጅነት በመቅረብ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በእርግጥ እነዚህ የፀረ-ሙስና ታጋዮች ትግሉን ሲያካሄዱ እንቅፋት አልገጠማቸውም ማለት አይደለም፡፡ በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፈዋል፡፡ ጥቆማ በማቅረባቸው እንኳን ከዛቻም አልፎ የግድያ ሙከራና ሀሰተኛ ውንጀላ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ በምግብ ለመመረዝ የተደረጉ የሙሰኞች ጥረትም ሳይሳኩ ቀርተዋል፡፡ እነዚህ ለአገራቸውና ለህዝባቸው ታማኝነታቸውን ያረጋገጡ የፀረ-ሙስና ትግሉ ጀግኖች ግን አሁንም በጥንካሬ ሙሰኞችንና ሙስናን የማጋለጥ እንቅስቃሴያቸውን በፅናት እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ተዲያ በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ መልካም አርአያ በመሆናቸው ለሥነ-ምግባርና ለፀረ-ሙስና ሽልማት እውቅና በቅተዋል፡፡

ሌላው መልካም ዜጋ የመልካም ሥነምግባር ትምህርትን በማስፋፋት እውቅና የተሰጣቸው አቶ ከፈለ ወ/ሰማየት ይበላሉ፡፡ አቶ ከፈለ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ውስጥ የተፈጸሙ የገንዘብ መጠናቸዉ በድምሩ ከ550 ቢሊዮን ብር በላይ በሆኑ ስምንት ጉዳዮች ላይ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን ያቀረቡ ግለሰብ ናቸው፡፡

አቶ ከፈለ ቀደም ብለውም ባቀረቡት ጥቆማ ላይ የተወሰደ እርምጃ ባይኖርም በዚህ ተስፋ ሳይቆርጡ እንደገና ዝርዝር የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን በማቅረብና በግል ክትትል በማድረግ የወንጀሉ ተዋናይ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎች በህግ እንዲጠየቁ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ የተፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችንና ለሙስናና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ አሠራሮችን በተለያዩ ሚዲያዎች በማጋለጥ የዜግነት ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ አቶ ከፈለ በአጠቃላይ የሙስና ወንጀሉን ማጋለጥ የጀመሩት ከ1993 ዓ.ም ገና የፌደራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኑ ሲቋቋም ሲሆን እስከ ዛሬም ድረስ የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች በመቋቋም ትግሉን አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ በእነዚህና ተያያዥ እንቅስቃሴያቸው ምክንያት ለሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሽልማት እውቅና በቅተዋል፡፡

ለዚህ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ሽልማት ከበቁ ሌሎች ግለሰቦች መካከል እንደዚሁ መምህር ዳንኤል ጌታቸው አንዱ ናቸው፡፡

መምህር ዳንኤል በቅሊንጦ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ መልካም ሥነ-ምግባር እንዲሰፍን በግላቸው ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ መሰረታዊ በሆነ መልኩ ሙስናና ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ድርጊቶችን የመከላከል ሥራ በህፃናትና ወጣቶች ላይ በሚሰራ ቀጣይነት ያለዉ የሥነ-ምግባር ግንባታ ሥራ ላይ የሚመሰረት ነው፡፡

በዚህም ረገድ መምህር ዳንኤል በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድን ለመፍጠር በግል ጥረታቸው በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ ለሽልማቱ ካበቋቸው መልካም ሥራዎች መካከል በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ለመፍጠር የሚያግዝ የማስተማሪያ ማንዋል ወይም መመሪያ ማዘጋጀት፣ ህፃናትና ወጣቶችን በመልካም ሥነ-ምግባር የሚያንፁ ከ100 በላይ የሆኑ አስተማሪ ጽሁፎች መጻፍ፣ "የትውልዱ እንቁ ምሳሌዎች" በሚል ርዕስ በቅንነትና በታማኝነት ሀገራቸውንና ወገናቸውን ያገለገሉ የ40 ታላላቅ ኢትዮጵያውያን የሕይወት ታሪክ ስብስብ እንዲሁም የምስልና ድምጽ ቅንብር (ቪሲዲ) ማዘጋጀት ይገኙበታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በተማሪዎች ላይ የሚስተዋሉ አሉታዊ የሥነ-ምግባር ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ የጥናትና ምርምር ሥራ፣ አሉታዊ የሚዲያ ተጽዕኖ በተማሪዎች ሥነ-ምግባርና ትምህርት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያግዝ ተግባራዊ የጥናትና ምርምር ሥራ አከናውነዋል፡፡ መምህር ዳንኤል በት/ቤቱ ውስጥ ያለውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለማሻሻል የሚያስችል የጥናትና ምርምር ሥራ፣ በትምህርት ተቋሙና ከትምህርት ተቋሙ ውጭ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሚገኙባቸው መድረኮች በመገኘት መልካም አስተሳሰብና በጎ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ሀሳቦችን በማቅረብ ባዘጋጁቸው ብዛት ያላቸው ጽሁፎች ከ1,000 በላይ ለሚሆኑ

መምራንና ተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ሰጥተዋል፡፡
መምህር ዳንኤል በመልካም ሥራቸው ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት ዕውቅና እና ሽልማት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በእነዚህና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ጉልህ የመልካም ዜጋ ተግባራትን በማከናወን ለአንደኛው የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሽልማት እውቅና በቅተዋል፡፡

ሌሎች መልካም ተግባራትን በማከናወና ለሽልማት የበቁ ግለሰቦች በጉምሩክ ኮሚሽን ውስጥ የሚሰሩ ታማኝ የህዝብና የአገር አገልጋዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች አቶ ጥላሁን ብዙአየሁ፣አቶ መንግስቱ በዳዳና አቶ አብዱ ይመር ናቸው፡፡ አቶ ጥላሁን በጉምሩክ ኮሚሽን ውስጥ በተሰማሩበት ቁልፍ የሆነ የሥራ መስክ ከፍተኛ የሆነ ፅናትና ቁርጠኝነትን በመላበስ ኃላፊነታቸዉን በባለቤትነት ስሜት በመወጣት አርአያ ሆነዋል፡፡ አቶ ጥላሁን ባከናወኑ መልካም ተግባራቸው በህገ-ወጥ መንገድ ከሀገር ሊወጣ የነበረ ከ12 ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ምንዛሬ እና ወደ ሀገር ውስጥ በኮንትሮባንድ ሊገቡ የነበሩ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን በግል ጥረት እንዲያዝ አድርገዋል፡፡ አቶ ጥላሁን የጥቅም ድለላ ለህገ-ወጥ ድርጊታቸዉ ተባባሪ እንዲሆኑ እጅግ የሚያማልል እጅ መንሻ በኮንትሮባንድስቶች ቢቀርብላቸውም ለህዝብና ለሀገር ጥቅም በመፅናት ኃላፊነታቸዉን ተወጥተዋል፡፡

አቶ መንግስቱ በደዳ በበኩላቸው የጉምሩክ ኮሚሽን ውስጥ በተመደቡበት ቁልፍ የሆነ የሥራ መስክ ከፍተኛ ፅናትና ቁርጠኝነትን ተላብሰው ኃላፊነታቸዉን ሲወጡ ቆይተዋል፡፡ አቶ መንግስቱ በህገ-ወጥ በተጭበረበረ ሰነድ በኮንትሮባንድ ለማሳለፍ ሲሞከር በመያዝ መንግስት ሊያጣ የነበረዉን ከ250 ሚሊዮን ብር በላይ ታድገዋል፡፡ አቶ መንግስቱ በሥራቸዉ ላይ እንዳሉ በህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች መደለያ ቢቀርብላቸውም ለግል ጥቅማቸው ሳይበገሩ በቁርጠኝነት አጋልጠዋል፡፡

አቶ አብዱ ይመር እንደዚሁ በጉምሩክ ኮሚሽን ዉስጥ በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ በከፍተኛ ታታሪነትና በመንፈሳዊ ቁርጠኝነት ግዴታቸውን በመወጣት መንግስት በተጭበረበረ መንገድ ከግብርና ቀረጥ ሊያጣው የነበረውን ከ90 ሚሊዮን ብር በላይ በመታደግ የዜግነት ግዴታቸውን ተወጥተዋል፡፡ አቶ አብዱ ህገ-ወጦች ከሞጆ



ጉምሩክ ጣቢያ በተጭበረበረ ሰነድ ያስገቡትን ሸቀጣሸቀጥ/ንብረት/ ሊያወጡ ሲወስኑ ክትትል አድርጎ እንዲጋለጡ በማድረግ ህገ-ወጦቹ በህግ የተጣለባቸዉን ግብርና ቀረጥ እንዲከፍሉ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በመልካም በታማኝነትና በመልካም ስብዕና




ያገለገሉ ግለሰቦች በእነዚህ እና በሌሎች እንቅስቃሴያቸዉ ላበረከቱት የዜግነት ጉልህ አስተዋጽኦ ለአንደኛዉ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሽልማት እዉቅና ሊያገኙ ችለዋል፡፡




በመጨረሻም ሽልማቱ ካገኙት መካከል በመንግስት ተቋም ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ኃላፊ በመሆን ኃላፊነታቸውን በፍጹም ታማኝነትና ታታሪነት ሲወጡ የነበሩ አቶ ካሳ ተሾመ ይገኙበታል፡፡ እንደሚታወቀው በመንግስት ተቋማት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ድርጊቶችን የመከላከል ሥራ የእያንዳንዱ ተቋም ኃላፊነት እንደመሆኑ መጠን ተግባሩን እንዲያስተባብሩ የተደራጁ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ድርሻቸዉ የላቀ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ በመሆን እያገለገሉ ያሉት አቶካሳ ተሾመ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

አቶ ካሳ የተቋሙን አሠራር ከሙስናና ብልሹ አሠራር ለመከላከል በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ ለመልካም ተግባራቸውም በተቋማቸዉ በተደጋጋሚ ጊዜያት እዉቅናና ሽልማትም አግኝተዋል፡፡ አቶ ካሳ በተቋማቸው ለእውቅናና ሽልማት ካበቋቸው ተግባራት መካከል በህገ-ወጥ መንገድ ሊከፈል የነበረ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ እንዲስተካከልና ከብክነት እንዲድን በማድረግ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማጥናት ለሙስናና ብልሹ አሠራር የሚያጋልጡ አሠራሮችን በማሻሻል የተለያዩ ህገ-ወጥ ድርጊቶችን የማጋለጥ ሥራዎችን ሰርተዋል፡፡ አቶ ካሳ በየትምህርት ዘመኑ ማጠቃለያ በብዙ ሺዎች ለሚቆጠሩ ተመራቂ ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በማዘጋጀት በተማሪዎች መካከል የጥያቄና መልስ ፕሮግራም በማዘጋጀት የተማሪዎችን የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ግንዛቤ በማሳደግና ሥነ-ምግባርን በማስፋፋት እንዲሁም ሙስናን በመከላከል የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱ የተቋሙ ሠራተኞች የሽልማት ፕሮግራም በማዘጋጀት ሠራተኞቹ ለተሻለ ሥራ እንዲነሳሱ የበኩላቸውን ጉልህ ድርሻ ተወጥተዋል፡፡

አቶ ካሳ ከተቋማቸዉ አልፎው ለሌሎች የሥነ-ምግባር መኮንኖች አርአያ የሆነ ተግባር በማከናወናቸው ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በአንደኛው የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስ ኮሚሽን ሽልማት ላይ እውቅና ያገኙ ታታሪ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና መኮንን ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የፌደራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንደዚህ አይነት የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ዕውቅናና ሽልማት ማዘጋጀት መቻሉ በራሱ ለቀጣይ የፀረ-ሙስና ትግሉ ጠቃሚ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በእርግጥ ሥነ-ምግባርን በማስፈንና ሙስናን በመከላከል ረገድ በርካታ ሥራዎችን የሰሩ ግለሰቦች፣ ተቋማትና የህብረተሰብ አደረጃጀቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ኮሚሽኑ እንዲህ ዓይነቱን ማበረታቻ መጀመሩ በራሱ አንዱ የፀረ-ሙስና ትግሉ ማጠናከሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ጊዜያት በጋራም ሆነ በተናጠል እንዲሁም እንደ ተቋማት የተጀመሩ የፀረ-ሙስና ትግሎች ሊጠናከሩ ይገባል፡፡ በተለይ ኮሚሽኑ በ2012 በጀት ዓመት በግንባር ቀደምትነት ለይቷቸው ለሽልማት ያበቃቸውን ግለሰቦች አርአያ በመከተል ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል መልካም ሥነ-ምግባር በማስፈንና ሙስናን በመከላከል ረገድ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት ይገባል፡፡

የህብረተሰብ አደረጃጀቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ኮሚሽኑ እንዲህ ዓይነቱን ማበረታቻ መጀመሩ በራሱ አንዱ የፀረ-ሙስና ትግሉ ማጠናከሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ጊዜያት በጋራም ሆነ በተናጠል እንዲሁም እንደ ተቋማት የተጀመሩ የፀረ-ሙስና ትግሎች ሊጠናከሩ ይገባል፡፡ በተለይ ኮሚሽኑ በ2012 በጀት ዓመት በግንባር ቀደምትነት ለይቷቸው ለሽልማት ያበቃቸውን ግለሰቦች አርአያ በመከተል ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል መልካም ሥነ-ምግባር በማስፈንና ሙስናን በመከላከል ረገድ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት ይገባል፡፡